# እግዚአብሔር ይይልህ!



*አቶ ማሶ አሊይ በችጋር መክንያት ከሞተች ልጃቸው ሽብሬ ጋር (ምንጭ-ሎሳንጀልስ ታይምስ)*

ይህን ግፍ አይቼ እንዳላየ ዝም ብል፣
ታሪክ ምን ይዘግብ ህሊናዬስ ምን ይል?

የሚበላ ጠፍቶ አጥንትሽ የወጣው፣
በሰው ሰራሽ ችጋር እድሜሽ የተቀጨው፣
ገመድ ቃሬዛ ላይ እሬሳሽ ያረፈው፣
በእራፊ ነጠላ ፊትሽ ክፍን ያለው፣
እንኳንስ ፈጣሪ የማይታፈነው፣
ስቃይ አበሳሽን የአለም ህዝብም አየው።

በርሃብ ስትገረፍ የተመለከትከው፣
"አባዬ! እንጣ!" ስትል እጅህ እጥር ያለው፣
የአጥንቶቿን መግጠጥ በአይንህ ያስተዋልከው፣
የአንጀቷን መሰለብ በእጅህ የዳሰስከው፣
ነፍሷ ስታጣጥር ልብህ ባር ባር ያለው፣
ጥርሷ ችንክር ሲል እንባህ የፈሰሰው፣
አስከሬን እያየህ እንጨት ላይ ቁጭ ያልከው፣
አቶ ማሶ አሊይ ከቶ እንደምን ቻልከው?

ቆዳህ ተጨራምቶ ጅማትህም ገሮ፣
አእምሮህ ተሞልቶ በአዘን በእንጉርጉሮ፣
አንደበትህ ታስሮ እጅህ ተጠፍሮ፣
በመኖር ላይ ያለህ የሰቆቃ ኑሮ፣
ምን ፍኖት ፈጥረሃል ለመውጣት ከእሮሮ?

ህጻን አዛውንቱን በርሃብ እየጠበስክ፣
ጎድኑን ቅልጥሙን ግጠህና መጠህ፣
በመውዛት በማበጥ በመድለብ ላይ ያለህ፣
ዛሬም ሆነ ነገ እግዚአብሔር ይይልህ።

ስንቱን ረፍርፈህ ስልጣን ላይ ቁጢጥ ያልህ፣
ፍቅርን ነቅለህ ጥለህ ጥላቻን የተከልህ፣
መገጣጠም ትተህ መበታተተን የያዝህ፣
ቆመህም ሞተህም እግዚአብሔር ይይልህ።

የስስት የጉጉት ቆሌ ተጠናውቶህ፣
ከአረመኔ አገዛዝ በጥብቅ ተቆራኝተህ፣
ፓርላማ ሚኒስቴር ኮሚሽነር ሆነህ፣
ሕጻናት በጠኔ በመፍጀት ላይ ያለህ፣
ሳይውል ሳያድር አላህ ፍርዱን ይስጥህ።

ከጉረሮ ላንቃ ነጥቀህ እየወሰድህ፣
ስንቱን በችጋር ፍም ጠብሰህ እየበላህ፣
የቅጽፈት ኑሮህን በመኖር ላይ ያለህ፣
ወላዲት አምላክን በኔ ይሁንብህ፣
እንደዚች ሕጻን ልጅ አይቀርም መሞትህ፣
ግፍ ከሰራህባት መሬት ውስጥ መዋልህ።

ከግፈኛ አገዛዝ ባቡር ላይ ተሳፍረህ፣
በድርቅ በበሽታ በጠኔ እያሳበብክ፣
ሮጣ ሳትጠግብ ሽብሬን የቀጨህ፣
ሐዘን ውቂያኖስ ውስጥ ወልጇን የዘፈቅህ፣
ቆመህም ሞተህም እግዚአብሔር ይይልህ!


በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ጥቅምት ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.